# የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ ማንፌስቶ።

## ማንፌስቶ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ የአጭር ጊዜ ትዕልሙና እቅዱ የሚስተገብራቸው በሁለተናዊ መልኩ ገጽታ ጠንካራ ዜጋና የሚታፈር ሕብረተሰብ ለማነፅ አስተማማኝ ተቋማትን መዘርጋት ነው። ሀያል ነበርን ኃያልም እንሆናለን፣ለዚህ ደግሞ እውንታ ሕዝባዊ መሰረቱ ቁልፍ በመሆኑ መጭው ትውልድ በቅጥያ የሚያጎለብተውና የትውልድ ድርሻን በማከል እረጅሙን የኢትዮጵያዊነት ታሪካችንን በተሀድሶ መገንባት ነው፤በኢትዮጵያችን ውስጥ የሚገነቡት ፓለቲካው ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ዘርፎችና የመከላከያ የደህንነትና ፓሊስ ሠራዊት ኃይል ተቋሞች ደረጃ በደረጃ በሕገ መንግስቱ መመሪያ በማዋቀርና በማደራጄት በሕዝብ ዘንድ በጥልቀት ስር በሰደደ መቆላለፍ ጎልብቶ የሕዝባችነን ሁለንተናዊ ችግሮች በሂደትና ቅድም ተከተል መፍትሔ እንዲገኝላቸው አንዱ ተቋም ከሌላው ከአንዱ ክፍለሀገር ለሌላው ቅርብ ግንኙነትና መረጃ በመለዋወጥ መደጋገፍ ወሣኝ ነው፣ቀልጣፋና ሕዝባዊ አመኔታን  አዳባሪም በመሆኑ ሕዝባችን ከዳር እስከዳር ለህልውናው ቀዳማይ እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ስለሚያስችል አንድነቱን ይበልጥ ያሣድጋል፣የነዚህ ተቋማት ሕዝባዊነት ይዘት ከትውልድ ትውልድ በእርጋታና ሕዝባዊ ይሁነታ በአወንታዊ ድልድል ዳብሮ ሲሸጋገር አኩሪ የፓለቲካ ባህል በማዳበር ኩሩ ዜጋና ማሕበረሰብ (ሕብረተሰብ)መገንባት ቁሣዊ አላማችን ነው።ነገር ግን ቀደምት ጉዳይ ቀዳማዊ ነውና፣የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ በቅርብና ሩቅ ታሪካዊ ፀረ ኢትዮጵያዊነት ኃይሎች ሁለንተናዊ ድጋፍ በማግኜት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት በተያያዘው ቅጥረኛ የባዕዳን ሎሌ ሕዝባዊ ወያኔ ሀርነት ትግራይ (ሕዋአትን)በተናጥል፤ውስጥ በቀል ፀረ ኢትዮጵያዊነት ኃይሎችና ግለሸቦችን በጅምላ ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት ሰፊው ሕዝብ ከዳር እስከዳር ለወሣኝ ድል እንዲበቃ በማደራጄት ሀገርና ሕዝብ የማዳን ትግል የሚጠይቀውን ግዙፍ መስዋእትነት ለመክፈል የስነልቦና የመንፈስና የአካል ዝግጁነት አጠናቆ ሲታገል የቆየ እንቅስቃሴውን በአዲስ መልክ በሀገራችን ምድር ከወያኔ ጋር እየተፋለመ ነው።ዘላቂ ፋይዳ ያላስጨበጠው ያለፉትን ረጅም ትግሎች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በተከሰቱበት ታሪካዊ ድባብ ውስጥ ብቻ በአጽንዎት በመመርመር በተለያየ ተቃዋሚ ድርጅቶች ዘንድ የተከሰቱ ድክመቶች እንዳይደገሙ በከፍተኛ ጥንቃቄና ተአድሶ በማድረግና  በመተግበር የኢትዮጵያ ሕዝብ የመሪ ያለህ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ እርሾ ትግሉን እንደተያያዘው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም በቅርብ ነቃሽነት አስተማማኝ ሕዝባዊ መሰረት በመሆን ከገባንበት የጠላቶቻችን፣ነበልባል ቀለበት መውጫው ብልሀት በውል በማመንጨትና በመተግበር ትግሉ ለማያዳግም ወሣኝ ድል እንዲበቃ ሕዝባዊ ክንድ ማሰባሰቡ ግድ  ነው፣ለዚህም ነው ከወያኔ መደበኛ ሠራዊትም በመክዳት አርበኛ ሠራዊቱን እየተቀላቀሉ የሚገኙት በቅረብም በሩቅም ያሉ ታሪካዊ ጠላቶቻን በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየተፈፀመ ለሚገኜው ዓለም አቀፍ ወንጀሎች ከአደባባይ ዝምታ በአሻገር ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የረጅም ዘመናት ህልማቸውን በሀገር በቀል ጠላቶቻችን ጉዳይ አስፈጻሚነት በስውርና ሰንካላ ሽፋን በመስጠት፣ለሚያደርጉት ንቁ  ተባባሪነት እራሣቸው የሚደመሰሰው፤በኢትዮጵያ አምላክ አዝማችነት በዛሬዎቹ ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን ቁርጠኝነትና የትግል መሪነት በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሰንሰለት በአንደነት እስከጠረፎቻችን በተዋረድ በኅበዝ አለቃነት ዘብ ቁሞ ያለጥርጥር እፁብ ድንቅ የሕይወት መስዋዕትነት ለመክፈል በሚጠይቅ ማንኛውንም ዓይነት አልሞት ባይ ተጋዳይነት ሕብረ ብሔር ተጋድሎና ሰልፍ አማራጭም በማይገኝለት ሕዝባዊ ሕብረት ብቻ ነው።የጠላቶቻችን መንጋ ሰፊና በውስብስብ ተሳትፎ የታጀበ በመሆኑ ለዚሁ አንፃራዊ ሕዝባዊ ቅንጅትና የሰከነ ወገናዊ ዝግጅት የግድ ይሏል። የኢትዮጵያዊነት አለኝታና መከታ ከኢትዮጵያ አምላክ ጎን እንደቀደምት ጀግኖች አያቶቻችን የዛሬው ትውልድ ልጆቿ ብቻ ናቸው፤የሚተገበረው ከባድ ኃላፊነት የኛ በመሆኑ ቁሳዊ መዋዕላዊ ዲፐሎማሣዊ ሥራወችና

ሞራላዊ ድጋፎች ከእያንዳንዳችን ለእያንዳንዳችን ብሎም በጣምራነት ትግሉን በመሪነትና በሕዝባችን ሙሉ ተሣትፎ እየታገለና እያደረጀ ለሚገኘው በኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ ሕብረ ብሔር ማዕከላዊነት ማሰባሰቡ ሕዝባዊ ሰፈሩን ከማጠናከር ባሻገር የማንቆጣጠረው አይቀሬ ኸከት እንዳማይኖር በእርገጠኛነት ለመተንበይ ያስችላል።በመላው ኢትዮጵያን ዘንድ እንደሚታወቀው ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የዋኋላ ሁዋላም ሀገራችንን የጦርነት አውድማ ለማድረግ ሁለንተናዊ ዝግጅቱን ያጠናቀቀው ዘረኛውና የባዕዳን ጥገኛ ቅጥረኛው ሕወሀት የሀገሪቱን ሀብቶች በብቸኝነት በመዳፉ ከማዋሉ ባአሻገር ከባዕዳን መንግስታት በገፍ የሚጎርፍለት ገንዘብ በአሸባሪነት ሤራወቹ የሚሰለፉለትን ቅጥረኛ ባእዳን ወታደሮች እንዳመቻቸ መገመት አያዳግትም፤ለወያኔ ሎቢስቶች ፈረነጅ ቀጣሪዎቹ በተለያየ መድረኮች እዳቀረቡለት ሁሉ ቅጥር ወታደር ተቋማትን አያውቁም ብሎ መገመት የዋህነት ነው፤ይኸን ሀገርና ኽዝብ ለማጥፋት በእብሪት የተወጠረ ቡድን ብቻውን ሣይሆን ከባዕዳን ኃይሎች ጋር ጣምራ ግንባር እንደፈጠረ ለእምንት ያህል ስንዘነጋ ሕዝባዊን ሰፈር በጠላቶቻችን ዝግጅት በአንጻራዊ መልኩ በማደራጀትና በማጎልበት ለዳግማዊ አድዋ የማያዳግም ድል እንዲበቃ ግድ ይሏል፤በመሆኑም የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ ፍንትው አድርጎ በአስቀመጠው በአጭር ጊዜ ፓለቲካዊ ትልምና ተግባራዊ ሂደት ሀገራችንና ሕዝባንን ከዘረኛውና ቅጥረኛው ሕዋሀት ጥፋት በከፍተኛ ሕዝባዊ ክንድ በመከላከል ብሎም ኢትዮጵያዊነት በወያኔነት መቃብር ላይ በአሸናፊነት በመቆም የምንነታችን መግለጫ አርማና ምልክት አረንጓዴ ብጫ ቀይ ሕብረ ብሔር ሰንደቅ ዓላማችንን ማውለብለብ ግድ ነው።አይቀርምም።ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያን ባህልና ታሪክ ሸምግልናን ያማከለ ሕብረሰባዊነት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ (ኢሕ አግ ዘብ )ኢየኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና አንድነት እንዲሁም የግዛት ሉዓላዊነትና ዳር ደንበር ለማስከበር የቁርጥ ቀን ጀግኖች ኢትዮጵያዊያንን በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ ሕዝብ ፊት ለወሣኙ ድል የሚያበቃው ትግል የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ቃል ኪዳን ገብተናል።በቅጥረኛው ወያኔ ሀርነት ትግራይ ሕወሀት ትግራይ)ጉዳይ አስፈፃሚነት በታሪካዊ ጠላቶቻችን የተቀነባበረው ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ይህውም ኢትዮጵያዊነትን ከምድረገጽ እንዲጠፉ የተዶለተው ሤራ በጀግኖች ኢትዮጵያዊን ደምና አጥንት በመክሸፉ ዘለቄታዊ ሰላም በሀገራችን ለማስፈን በቁርጠኛነት ትግሉን ዳር ላማድረስ ትንቅንቁን ተያይዘነዋል የኢትትዮጵያ ሕዝብ ባለ ብዙ ነገድና የዳበረ ባሕል አኩሪ ታሪካችንን ያገናዘበ ሕዝባዊ የፓለቲካ ስርአትና ስነ መንግሥት ለዚሁም የአላት መሠረት አስፈላጊው ተቋሞች በየ ክፍለ ሀገር ግዛቶች አቁሞ እንደፈቀደ) በተዋረድ እንዲቆረቆር ኢሕ አግ ዘብ)አንዱና ቀዳማዊ አጀንዳው ነው።ይህ በእንዲህ እንዳለ የክፍለሀገረ ሕዝብ የራሱን አስተዳዳሪ ሀገር ሕዝቡ አወዳድሮ በመምረጥ በውክልናም በቀጥታ ተሣትፎም የፓለቲካ ባለቤትነት በእጁ እንዲሆን በቁሣዊ ደረጃ እንዲገነዘብ ማድረግ ቁልፍ የፓለቲካ ግባችን ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ፣ኢሕ አግ ዘብ)የትግል አርማ የትግል ሰንደቅና መርሕ ኢትዮጵያዊነት እና ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው።ኢትዮጵያዊነት ሰብአዊነት ነው፤ኢትዮጵያዊነት የሕግ የበላይነትና ፍትሕ ነው።ኢትዮጵያዊነት የሰው ልጅ ለሰው ልጅ ፍቅር ነው።ኢትዮጵያዊነት ታማኝነት ነው።ኢትዮጵያዊነት ሐይማኖተኛና ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረበት ዕውነተኛነት ማለት ነው። ኢትዮጵያዊነት ለዳር ደንበር ለግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት ቀናዓዊነት አትንኩኝ ባይነት ጀግንነትና አርበኝነት ነው።ሁሉንም ዓየነው የቀረን የሀገሩን ሰርዶ በሀገሩ በሬ እንዲሉ ኢትዮጵያዊነት እፁብ ድንቅ ባህላችንና የተባ ታሪካችንን ዕንቁ ፍልስፍና ነው፣የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ገላጭ ዘብ ኢሕ አግ ዘብ ጎጥ ጎሣና ሃይማኖት ሣይለይ ሕብረ ብሔር ኃይል በኢትዮጵያ ሕዝብ ማዕከላዊነት ፍርጥም ያለ ሕዝባዊ ሠራዊት በማሰለፍ ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ያሰፈሰፈውን ኩታ ገጠም የጠላት መንጋጋ

ዓለም አቀፍ ሜራ ለዝንተ ዓለም ከሀገራችን ምድር መጥፋቱን ያረጋግጣል፤ትዮጵያዊነትን ፓለቲካዊ ሰንደቅ በማንገብ ለመስዋዕትነት የተሰለፈው የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ሠራዊት፣

(People,s Army of liberatine Ethiopia)የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትና ሉዓላዊነት የሕዝቧን ነፃነትና ብሔራዊ ክብረ ሞገሷን ጠቀሜታዎችንና ሁለንተናዊ የኢትዮጵያዊነት ደህንነት ያለምንም መመንታትና አዕመሮአዊ መቆጠብ በግንባር ቀደም ደጀንነት በመቆም ለመጠበቅ በቁርተኝነትና በተጠንቀቅ ተሰልፈናል።የቀደምት ክፍለ ሀገሮች ውሰጡ መልከዐ ምድር ወሰኖችና የግዛት አስተዳደር መጠሪያ ስማቸው፣ሸዋ አሩሴ ሐረርጌ ትግራይ ወሎ ሲዳሞ ኢሉባቦር ወለጋ ከፋ ጎጃም ስሜንና ቤገምድር ጎሙጎፋ ጎጃም ባሌ ባህረነጋሽ)በቅደመ ወያኔ ሕገመንግስቶች እንደተደነገጉትና እንደተዋቀሩት መከበራቸውን በፍጹምነት እንታገላለን።በዚህና ሌሎችንም የትግል ሂደቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ የሁንታና ሕዝብ ውሣኔ መሰረት በማድረግ ነው።በረዥም አኩሪ ባህላችንና ታሪካችን የሕብረተሰባችን ፓለቲካዊ የዘውድ ስርዓት (ደርግም ጨምሮ)በእውቀትና ፍልስፍና እንዲሁም በተለየ እደጥበብ ሙያ ዘርፎች ተሰጧዊ ብቁ ተመክሮ ያላቸውን ዜጎች አቅፎ በመንግስታዊ ፓሊሲዎቻቸው አላካተቱም።ብቁና ንቁ ሕዝብ ለአንድ ህብረተሰብ ልማትና እድገት አማራጭ የለውም ለወደፊቱ አዲሱ የታሪካችን ምዕራፍ ግን ካለፉት ስህተቶች በመማር እያንዳዱ ዜጋ ያለውን ተሰጦና ችሎታ በየአካባቢው በተዋረድ እሰከብሔራዊና ማዕካላዊ ደረጃ በሕብረተሰባችን ፓለቲካዊ ብሩህ ሂደት ከፍተኛውን ሥፍራ እንደሚይዝ አያጠያይቅም፣የወደፊቱ ወርቃማ ዘመን የአለት መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።በኢትዮጵያዊነት ባህልና ታሪክ አኳያ የተማረና የተመራመረ ሕዝብ ለወገኑና ለሀገሩ ሕዝብ ሉዋላዊነት ቀናኢ ነው፤ይኸን እሴት(ሕዝባችን)በፍጹምነት.በምናከብረው ሕገመንግሥት እንዲታደግ የኢሕ አግ ዘብ ቃል ኪዳን ማሕተብ ነው።

በሕብረተሰባችን ፓለቲካዊእና ኢኮኖሚያዊ ማህበረሰባዊ ገጽታወች ሁለንተናዊ እድገት ለመቀየስና ለመተግበር በተለያይ የዕውቀት መስኮች ትምህርትና ተመክሮ ያዳበሩ ኢትዮጵያዊያን ሊቃውንት ዕድ ጥበብተኞች በሕግና ፍትህ በዳኝነት በጥብቅና በአስተዳደር በጤና ሙያ በወታደራዊ ሣይንስ በኢኮኖሚክስ በመምሕርነት በመሀዲስነት ሙያ በመብራት ኃይል መንገድና ከተማ ቀያሽነት እርሻ ወዘተ በግብርና በከብትና እንስሣ ዕርባታ ወዘተ የተካኑ ዜጎች በሕገመንግስት የተላበሱትን ጽኑ መብትና ግዴታ በመጠቀም በሙሉ ነጻነት ሲሣተፍ ብቻ ነው፣ይህን ቁሣዊ መልክ ለማስያዝ የኢትዮጵያ አንቱ የተባሉ አረጋውያን መማክርትን ያቀናጀ ኮምሽን ማዋቀር ግድ ነው።ለዚህም በቂ ዝግጅት ጥናትና ምርምር ቢጠይቅም ማለፊያ ጅማሮ የማዕዘን ድንጋይ ተጥሎአል።የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ ዘለቄታማ የፓለቲካ አመራርና አወቃቀር ባህል በሕዝባዊ ይዘት በማነጽ መጭው ትውልድ በቀጥታ የሚያጎለብተውና በክስተቶች አስገዳጅነት በሕገ መንግስቱ መሠረት የሕብረተሰባችንን የወል ጠቀሜታወችና የሕዝብን ለዓላዊነትና ደህንነት በማይፈታተን መልክ አስፈላጊነታቸው የሚታመን ነገሮች በመጨመር ወይም በማሻሻል በሁሉም አቅጣጫ ትውልዳዊ አስተዋጽዎ ተከታታይነት እንዳይዛነፍ የአለት መሠረት መጣል ረዥሙ ግባችን ነው።

በማያሻማና በማያጠራጥር ሁኔታ የዕሴቶቻችን ዕንብርት ከደቂቅ እስከ ሊሕቅ የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው። ከላይ በተጠቀሰው አኳያ እነዚህ ታላላቅ ኢትዮጵያወን ምሁራን በባህላዊና ዘመናዊ ትምህርት ታላላቅ የሼሪያን ሙስሊምና የክርስትና ሐይማኖቶች አባቶችና ተከታይ መሪዎች ታላላቅ አዛውንቶችን የሲቭክና ፓለቲካ ድርጅቶችን ያቀፈ ጊዜአዊ የሽግግር መንግሥት እስከአምስት ዓመት ድረስ በአመራር እንዲቆይ በምድረግ ሕዝብና ሀገርን በፍጹም አስተማማኝ ሁኔታ ማረጋጋት ግድ መሆኑን እናምነለን። በዚሁ ጊዜአውዊ የሽግግር መንግስት ጥላ ስር ዕርቀ ሰላም በሕዝበ ለሕዝብ ኦፊሰላዊ በማድረግ ለተግባራዊነቱ አስፈላጊውን ሁሉ እናከናውናለን፤በዚህ ሂደት የሕዝባችን የተለያዮ ጎሣዎች የቅርብና

ሩቅ ችግሮችና መጠየቆች በሚመቻቸው ሕዝባዊ ተቋሞች በጥንቃቄ ይጠናል፤በወል ጠቀሜታ ላይ በሚያተኩሩ ጉዳዮችና በሕዝብ ነፃነት  አንድነትና ሉዓላዊነት እንዲሁም የግዛት ዳር ደንበር ለድርድር የማይደረግ በቂ ምላሽ እንዲገኝ  ሁሉም ወገን በኢትዮጵያውነት መንፈስ እንዲጥር ይደረጋል፤የመገናኛ ብዙሀን ሚና ከታሪክ አዋቂ ምሁራንና ታሪካችንን በተካኑ ጥንታዊ አፈታሪኮችን ዛሬም በሚያስተምሩ አረጋውያን ዜጎች እየታገዘ ሕዝባችንን ማስተማርና በቂ ግንዛቤ በማስጨበጥ ሙያዊና ዜጋዊ ግዴታቸውን በከፍተኛ ደረጃ በመወጣት ኃላፊነት ይኖረዋል። ሕዝብም በሰፊውና በነጻነት እንዲወያይ መድረኮች ሁሉ ነጻ ናቸው፤የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ በኢትዮጵያዊነት ላይ ወንጀል ያልፈጸመ አንጋፋ የጦር መኮንኖችና የጦር አለቆች በመከላከያ ተቋሙ በማካተት የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞችና መደበኛው የኢትዮጵያ ጦር ኃይሎች አየር ኃይል ምድር ጦር ፓሊስ ሀገርና ሕዝብ ደሕንነት ወዘተ ጣምራ ኮሚሳሪያት በጊዜአዊ የሽግግር መንግስት ስር በማደራጀትና በማዋቀር የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ያለ ምንም ማመንታትና መቆጠብ በቅድመ ወያኔ ስርአቶች የተከበሩትን የአየር የባሕር የብስ ወሰኖች መከበራቸውን ያለምንም ድርድር ያረጋግጣል።ከማንኛውም የኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰላምና መልካም ወዳጅነት ከመኖር ባሻገር  የዓለም አቀፍ ውጭ ግንኙነቶች በዓለም አቀፍ ሕጎች ውሎችና ደንቦች መሠረት ቀና መልክ እንዲይዙ ይጥራል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትዳር ደንበርና የሕዝቧን ነጻነት በሚፃረር መንገድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ውክልና በሌለውና ከጸረ ኢትዮጵያውነት መንግስት ጋር በመተባበር ሕወሀት ወያኔ የተፈራረመውንና የተደራደራቸው ዉሎች በሙሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ውክልናና ይሁንታ ያለው የሽግግር መንግስት ዘንድ ውድቅ ናቸው፣የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ በሽግግር የኢትዮጵያ መንግስት የሚወሰዱ እርምጃዎችና ትዕዛዞችን ያለ ምንም ማቅማማት ይፈጽማል፤ይኅ በእንዲኅ እንዳለ የሽግግር መንግሥት በውስጥ የህገመንግሥት አርቃቂ ኮምሽን በማቋቋም የሚተገበረው ሕገመንግሥት መንደፍና ረቂቁ በሕዝብ ውሣኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋሚ መተዳደሪያና የኢትዮጵያ ዜጎች ትውልደ ኢትዮጵያም)ማንኛውም መብቶችና ግዴታዎችን የሚያስከብርና የሚጠብቅ ሕግ እንዲሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ፣(ኢሕ አግ ዘብ) ያረጋግጣል ኢትዮጵያውያን ዜጋ ሁሉ በስደት ሀገሮች ለሚገኙትም ትውልደ ኢትዮጵያዊያን የግለሰቦች መብቶች በኢትዮጵያ ሕገመንግሥት በጽኑ ይከበራል፣የኢትዮጵያሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ የእያንዳንዱ ግለሰብ ዜጋ የእያንዳዱ ነገድና ጎሣ የእያንዳንዱ ሐይማኖት ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ በሕዝ ውሣኔ በሚጸድቀው ሕገመንገሥት በፅኑ መከበሩን አስፈላጊና የሚመለከታቸው መንግታዊ ተቋሞች በተዋረድ እንዲዋቀር መሥረት በመጣል ለተግባራዊነትና ተፈጻሚነት በሁለገብ ክትትል በእርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብ የፓለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት በአደባባይ ያስደመድማል፣ኢሕአግዘብ በኢትዮጵያዊነት ርዕዮተ ፍልስፍና እና የአርነት ትግል ዱካና መመሪያ ሰንደቅ በማንገብ በፓለቲካ በኢኮኖሚ በማህበራዊ ዘርፎች በአጭር የትግል ሰንጠረዥ የኢትዮጵያን ትንሣየ በሕዝብ የስልጣን ባለቤትነት የፓለቲካውን ኃይል ከፀረ ኢትዮጵያዊነት ሕወሀት እጅ በማስለቀቅ ሕዝባዊ ተዓድሶ ብሎም መካከለኛና ረዥሙን የዕድገትና ልማት መርሐ ግብር በጥናትና ምርምር በሚደገፍ ሂደቶች መከናወኑንና በሕዝብ ማዕዘንነት ላይ መታነጹን ማረጋገጥ ነው።

ክፍል ፣)ፓለቲካዊ ዘርፍ

ሀ)የአጭር ጊዜ ወሣኝ ፓለቲካዊ ትልም ኢላማና ወሣኝ ግቦች፤በኢትዮጵያ ሕዝብ ማዕበልነት ኢትዮጵያዊነትን ከጠላቶቻችን ጥቃትና ጥፋት በመከላከል ሕዝብነታችንና ሰውነታችንን ለእልፈት እያመቻቸ በጎጠኝነት ፓለቲካ መርዝ ትውልድ እያካለለ የሚገኜውን የዓለም አቀፍ ጸረ ኢትዮጵያነት ሴራ እንደራሴ ሕወሀት ኢትዮጵያ አፈር እንዳይቀበር ከኢትዮጵያ ምድር ለሽታም እንኳን እንዳይቀርና እንዳይታይ ጨርሶ ማጥፋት ነው፤ለዚህ ተፈጻሚነት የፓለቲካው ልጥጥ አባል ወታደራዊ እንቅስቃሴአችን ግዝፉን ድርሻ በሀላፊነት ለመወጣት የቆየ ትግሉን በተአድሶ በሀገራችን ምድር

ግብግቡን እንደተያያዘው ይገኛል።ሌሎች ኃይሎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ነጻነት አንድነትና የሀገር ሉዓላዊነትና ብሔራዊ የወል ጠቀሜታዎችና ደሕንነት በማያደራድር ሁኔታ ሕዝብና ሀገርን ከጠላቶቻችን ጥቃትና እልፊት ለመከላከል መመዘኛና መለኪያ አቋማቸው ያደረጉ የትግሉ አካል ናቸው፣የሚመለከተውም ውስጣዊ አካል ዝርዝር ሂደቱን በሀላፊነት እንዲወጣ ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፣

ለ/ የኢትዮጵያን ጥንታዊ መልካዐ ምድር አቀማመጥና ይዞታን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ደንበር ኮሚቴና ሌሎች የሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋሞች ጋር ሰፊ ጥናትና ምርምር ሥራዎችን ለይገባኛል ሕጋዊና ጥንታዊ ባለቤትነት ጥያቄዎች ዝግጅት ከማድረግ በተጨማሪ ቅድመ ወያኔ የየብስ ግዛት ብሔራዊ የአየር ክልል ታሪካዊ የባሕር ወሰኖችና ሁለንተናዊ ሉዓላዊነት ያለምንም ድርድር በኢትዮጵያውያን መታጠር እንዳለበት ዕውን ማድረግ ነው።

ሐ/የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሁንታ ያገኘ፣ሁሉንም ክፍለ ሀገሮች ያቀፈና በአብዛኛው ሕዝብ የተወከሉ የየጎሣ መሪዎች ወይም ተወካዮችን ያካተተና የሚሣተፉበት የሽግግር መንግስት እስከ አምስት ዓመቶች ያከል በመሰየም ሰፊ ሕዝባዊ ምርጫ (ፓረላማ እንደራሴዎች)ማካሄድ።

መ/በሽግግር መንግስትና በሕዝብ እንደራሴዎች ፓርላማ መደጋገፍ ሕገመንግሥት ተነድፎና ረቅቆ በሕዝብ ውሣኔ የሚጸድቀው ሕገመንግስት የሀገሪቱ የበላይ ሕግና ፍትህ በማይናወጥ መሰረት ማነጽ በሕዝብ ውሣኔ የጸደቀው ቋሚ ሕገመንግስት እያንዳንዱ ዜጋ መብትና ግዴታ የእያንዳንዱ ነገድና ጉሣ ባህልና ታሪክ ሃይማኖቶች ሁሉ በኢትዮጵያ ምድር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአቻ ደረጃ ይከበራል በሕግ አምላክ ሌላ መጤ ደዌ በቃ።

ሠ/በጎጠኝነትና ጎሰኝነት ፓለቲካ ደዌ የተበከለው ኢትዮጵያዊነት እንደጎህ ጠርቶ እንዲወጣ ዕርቀ ሰላም ከሕዝብ ለሕዝብ ውይይት ከሀገር አድማስ እስከ አድማስ እስከ ስድስት ወሮች በሚፈጅ ጊዜ በሽግግር መንግሥቱና ፓርላማው ቅንጅት ዘመቻ በአረጋዊያን ወገኖች በከፍተኛ የሀይማኖት መሪዎችና ታላላቅ ኢትዮጵያዊያን ሊቃውንትና መላው ሕዝባችን ተባባሪነት ንቁና ትጉህ ኩታ ገጠም ቅንጅት የኢትዮጵያዊነት ሕላዌ ሕይወት ዳግማዊ ትንሣኤ እንዲያደርግ የኽን አብይ አጀንዳ መተግበር ግድ ነው

ረ/ውጩና ዓለም ዓቀፍ ግንኙነቶችን በሚመለከት ኢትዮጵያ የሌሎች ሀገሮች ሕዝቦች በሰላምና መልካም ግንኙነት እንዲኖሩ በተደነገገ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ሕጎች በማክበር ከሚታወቁት አንዷ ነች፣ነገር ግን ጨዋ መሣይ በሸንጎ እንዲሉ የትልቅ ትንሽ መንግሥታት ጋር በነበራት ጥንታቄ የጎደለው ግንኙነት የኢትዮጵያዊነትን ሕልውና ለማጥፋት ለዘመናት በስውርና በገሀድ ሲታናኮሉን እስከዛሬም እየተዋጉን ያሉ ዓለም ዓቀፍ ወንጀሎችን መንግሥታት እነማንና ምን ምን መቼ በሕዝባችንና ሀገራችን ላይ እንደተፈፀመ በመፈፀም ላሉ ወንጀሎች በመረጃና ዋቢ ነቃሾች በማስቀመጥ ሕዝባችንን ግንዛቤ እንዲያገኝና ንቁ ውሣኔ በማድረግ ይወስናል፡ሰላምና መልካም ጉርብትና ወዳድ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በሰው ልጅ ፍቅርና መተሳሰብ መልካም ግንኙነቶች በአዎንታዊ እንዲቀጥሉ የተለመደ ጨዋነቱን አይነፍግም።

ክፍል 2/የኢትዮጵያን ኢኮሚያዊ ዘርፍ በጥልቀትና በስፋት በሙያው የተካኑ የኢትዮጵያ ምሁራን ልጇቿ አስተማማኝን ፈር እንዲይዝ እንደሚያደርጉ እምነታችን ወደርና ወሰን የለውም፤ነገር ግን እንደአደባባይ የሕዝብ ፊትነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ዘብ የኢኮኖሚ ምንጭ የኢትዮጵያ መሬት በመሆኑ የኢትዮጵያ ምድር ግዛቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ የወል ሀብት መሆኑን ያለምንም ማመንታት ያምናል ይታደገዋልም።የኢትዮጵያ ሕዝብ የኢትዮጵያ መሬት ፍጹም ባለቤት ነው።የገጠርና ከተማ መሬቶች ዘርፈ ብዙ ጥናቶች አካቶ በሚፀድቀው ቋሚ ሕገ መንግስት በግልጥና ፍንትው ተደርጎ

ይዘረዘራል በተለይ የገጠር መሬት ይዞታ በአንዳንድ ክፍለ ሀገሮች ውስብስብና ረጅም ታሪክ ያላቸውን፣አካባቢዎች ባህልና ወግ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ ችግሮችን በጥልቀት የሚመረመርና ጥራቶችን ለሕገ መንግስት አርቃቂ አካል የሚያቀርብ ልዮ አጥኚ ኮምሽን በማዋቀር ከተለያየ የሚመለከታቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ሕዝብ ጋር ቀጥታ የስራ ግንኙነትና የቅርብ ውይይት የሚያደርግ ልዑካኖች እንዲሰማሩም ያደርጋል።ይኸ የሕብረተሰባችን ዘርፍ (ኢኮኖሚው)ከፓለቲካው ሌለኛው ክንፍ ጋር በመቆላለፍና መጣጣም ሕብረተሰባችን በሁለት ክንፍ እንደምትበር ወፍ ስለሚመስል በዚሁ ዘርፍ የብሄራዊ ኦዲት ኮሚሽን መዋቀር የልማትና ዕድገት ዕቅዶች ሂደት እናዳይዛንፍና ሥራዎች በንቁነትና ኃላፊነትን በመወጣት ይከናወናል።

ክፍል 3/ ማሕበራዊ ዘርፈ፣

አንድ ህብረተሰብ የሚታፈረውና ዕድገትና ልማቱ የሚመዘነው እያንዳንዱ ዜጋ በህብረተሰቡ ውስጥ ፓለቲካዊ ኢኮኖሚያዊ ግንባታ እንደአቅሙና ችሎታው በሚያስከትለው አወንታዊ ድርሻ በሚገኝም ፍሬአማ ውጤቶችና በሀገሪቱ ከርሰ ምድርና ከላይ የተንግለሉ ሀብቶች የወል ተጠቃሚ በመሆን የንሮ ደረጃው በአመርቂ ሁኔታ ላይ ሲገኝ ነው።የህብረተሰብ ጥንካሬ አንድና አንድ የዜጋዎች ጠንካሬ መሆኑን በሚገባ ስለምናምን አጀንዳችንና ግባችን ጠንካራ ዜጋና በሁሉም መስኮች ጠንካራ ህብረተሰብ መገንባት ነው።

ሀ/ትምህርት በማንኛውም ሕብረተሰብ በሁሉም ማህበራዊ ዘርፎች ሕሊናዊ ቁሳዊ ማደረግና መሻሻል የማዕዘን ድንጊያና ምሶሰው ትምህርት ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ሕዝብ ሁለገብ ተሣትፎ (እስልምና ሀይማኖት ሊቆችና የቤተክህነት ሊቃውንትን ያካተተ ባህላዊ ትምህርት በተለይም የኢትዮጵያን ኩሩና የተባ ታሪክ በኢትዮጵያዊነት ደም ሥር ፍልስፋና ከትውለድ ትውልድ ፍስቱ እንዳይዛነፍ።

የግዕዝ፣ስርዓተ.ትምህት፣ተነድፎ፣ይተገበራል፣ጥናት.እና.ምርምር(በየደረጃው)ያማከለና ኢትዮጵያዊነትን.ያገናዘበ ዘመናዊ የሣይንስና ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረገ ስርዓተ ትምህርት መንደፍ ግድ ይሏል፤በመሆኑም በሰከነ ዝግጅትና ዕቅድ ተግባራዊ እንዲሆን ኢትዮጵያዊያን ጠበብት ምሁራን ቁልፍ ሙያዊ ኃላፊነት በመሆኑ፣ኢሕ አግ ዘብ።ባዋቀረው ዲፋክቶ የትምህርት ተቋም ከወዲሁ በሁኔታወች አመችነት ሥራው ይጀምራል።

ለ/ጤና የጠንካራ ዜጋ ሌለኛው መስፈርት የተሟላ ጤናማነት ነው። ይኸን ለመተግበር ነባር የጤና ተቋሞች ሆስፒታሎች ክሊኔኮችና ፋርመሲዋች ከሕንፃ ተአድሶ እስከሕክምና ቴክኖሎጂ ወደ ዘመናዊ ቁሣቁሶች መሣሪያዎችና መድኃኔቶች አቅርቦት ስለሚጠይቅ የሚመለከተው መንግስታዊ አካል በሙያው ያሉና የነበሩ ሊቆች ኢትዮጵያውያንን በአውደ ጥናት በማቀናጀት መክሮ ዘክሮ የሚያስተገብር ጉዳይ ነው።

ሐ/ሌሎች ማህበራዊ ዘርፎች መገናኛ.(መንገዶች ድልድይ ሥራወች ወዘተ የመጠጥ ንፁህ ወሀ አቅርቦት፣ገዳማትና ታሪካዊ ቦታዎችና ቅርሶች አሰባሰብና አጠባበቅ እንዲሁም አያሌ ብዙ ማሕበራዊ ጉዳዩች በሂደት በሚመለከታቸው ተቋማትና በሚመለከታቸው ዜጎች ህብረትና ቅንጅት አስፈላጊው ሁሉ የከወናል።

አንድነት ኃይል ነው።